የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 52
ADDIS ABABA, 5th August, 2026

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፱/፪ሺ፲፰

የትዕዛዝና ቁጥጥር እና የንብረት አስተዳደር ስርዓቶችን የደረጃ አወጣጥና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ ሪፐብሊክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ…………………………………………………………………..……..ገጽ ፲፱ሺ፱፻፶፮

**Content**

Proclamation No. 1439/2026

French Republic Loan Agreement to Support the Standardization and Digitalization of Command and Control of Asset Management Systems Project Ratification Proclamation No……………………………………………….......Page 19956

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፱/ ፪ሺ፲፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሳይ ሪፐብሊክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የትዕዛዝና ቁጥጥር እና የንብረት አስተዳደር ስርዓቶችን የደረጃ አወጣጥና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፶፬ ሚሊዮን ፮፻ሺ ዩሮ (ሃምሳ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሳይ ሪፐብሊክ መካከል ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1439/2026

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND FRENCH REPUBLIC

**WHEREAS,** the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and French Republic shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Fifty Four Million Six Hundred Thousand EURO (EURO 54,600,000) to Support the Standardization and Digitalization of Command and Control of Asset Management Systems Project, was signed on the 13th day of May 2026;

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፪ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የትዕዛዝና ቁጥጥር እና የንብረት አስተዳደር ስርዓቶችን የደረጃ አወጣጥና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ ሪፐብሊክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፴፱/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ግንቦት ፭ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶፬ ሚሊዮን ፮፻ሺ ዩሮ (ሃምሳ አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS,** the House of Peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 2nd Extra ordinary sitting held on 14th day of July, 2026;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "French Republic Loan Agreement to Support the Standardization and Digitalization of Command and Control of Asset Management Systems Project Ratification Proclamation No. 1439/2026".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement signed on the 13th day of May 2026 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and French Republic is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Fifty Four Million Six Hundred Thousand EURO (EURO 54,600,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

**ታዬ አፅቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 5th Day of August ,2026**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**